Montgomery County Fire and Rescue Service
Community Risk Reduction • www.mcfrs.org/mcsafe • X @mcfrs

አዲስ የካርቦን ሞኖክሳይድ አላርም ህግ ፣ ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።
ከ 2008 በፊት ለተገነቡ ቤቶች አዲስ መስፈርቶች። የበለጠ ለመረዳት፣ www.mcfrs.org/mcsafe

**የካርቦን ሞኖክሳይድ ደህንነት**

ብዙውን ጊዜ የማይታይ ገዳይ ተብሎ የሚጠራው፣ ካርቦን ሞኖክሳይድ የማይታይ፣ ሽታ የሌለው፣ ቀለም የሌለው ጋዝ ሲሆን የሚከሰተው (እንደ ቤንዚን፣ እንጨት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ፕሮፔን፣ ዘይት እና ሚቴን ) ያሉ ጋዞች ሙሉ በሙሉ ሳይቃጠሉ ሲቀር ነው። በቤት ውስጥ በጋዝ የሚሰሩ ማሞቂያዎች እና ማብሰያዎች የካርቦን ሞኖክሳይድ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ።

- የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርሞች ከእያንዳንዱ የመኝታ ክፍል ውጭ ባለው ማእከላዊ ቦታ እና በእያንዳንዱ የቤት ደረጃ ላይ መገጠም ይኖርባቸዋል ፤ በተጨማሪም ህጎች፣ ኮዶች ወይም ደረጃዎች በሚያዙት መሰረት በሌሎች ቦታዎች መገጠም አለባቸው። ለተሻለ ደሕንነት ፣ ሁሉንም የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርሞች እርስ በእርስ ያገናኟቸው። አንዱ ድምጽ ሲያሰማ (ሲጮህ) ሁሉም ድምጽ ያሰማሉ(ይጮሃሉ)።
- ስለ አገጣጠሙ እና የሚገጠምበትን የቁመት መጠን ለማወቅ የፋብሪካውን መመሪያዎች ይከተሉ።
- ብቃት ባለው የምርመራ ላብራቶሪ በኩል የተዘረዘረውን የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርም አይነት ይምረጡ።
- የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርም በሚጮህበት ጊዜ የሚደውሉበትን ስልክ ቁጥር ለማወቅ በአካባቢዎ ወደሚገኘው የእሳት አደጋ ቢሮ ድንገተኛ ያልሆነ የስልክ ቁጥር ይደውሉ እና ይጠይቁ።
- ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርሞችን ይፈትሹ ፣ በሚቀይሩበት ጊዜ የፋብሪካውን መመሪያ ይከተሉ።
- ባትሪው እንዳለቀ የሚጠቁም ድምጽ ከሰሙ፣ ባትሪው ማለቁን ይፈትሹ። ባትሪው ካለቀ ይቀይሩት ። አሁንም ድምጽ የሚሰማ ከሆነ ለእሳት አደጋ ክፍል ይደውሉ።
- የካርቦን ሞኖክሳይድ (CO) አላርም ድምጽ እንደሰሙ ወዲያውኑ ንፁሕ አየር ወደሚያግኙበት ከቤት ውጪ ወይም ወደ ተከፈተ መስኮት ወይም በር ይሂዱ። በቤቱ ውስጥ ያለ ሁሉም ሰው የት እንዳለ ያረጋግጡ። ንጹህ አየር የሚያገኙበት ቦታ ላይ ሆነው ለእርዳታ ይደውሉ እና የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች ወደ ቤት ለመመለስ እንደሚችሉ እስከሚነግሮት ድረስ እዚያው ይቆዩ።
- መኪናዎን ማሞቅ ከፈለጉ ፤ ከአስነሱት በኋላ ወዲያውኑ ከጋራዡ ውስጥ ያውጡት። የጋራዥ በሮች ክፍት ቢሆኑም እንኳ መኪና ወይም ሌላ በነዳጅ የሚሰራ ሞተር በቤት ውስጥ ሞተሩን አስነስተው እንዳይተዉ። የመኪናው የጭስ ማውጫ ቱቦ በበረዶ ያልተሸፈነ መሆኑን ያረጋግጡ።
- በበረዶ ወቅት እና በኋላ የልብስ ማድረቂያ ማሽን ፣ ምድጃ እና እሳት መሞቅያ የአየር ማስወጫቸው በበረዶ አለመደፈኑን ያረጋግጡ።
- ጀነሬተር ከመስኮቶች፣ ከበሮች እና ከአየር ማስወጫ ቦታዎች ርቆ ጥሩ አየር ባለበት ቦታ ላይ ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።
- በጋዝ ወይም በከሰል የሚሰሩ ግሪሎች ካርቦን ሞኖክሳይድን (CO) ሊያመነጩ ስለሚችሉ ከቤት ውጭ ብቻ ይጠቀሙ።

**የቤት ውስጥ ማሞቂያዎች**

የቅዝቃዜው ወቅት ከመግባቱ በፊት በነዳጅ የሚሰሩ ማሞቂያዎችን እና የእሳት መሞቂያዎችን በየአመቱ በባለሙያዎች ያስፈትሹ። የእሳት መሞቂያን በሚጠቀሙበት ጊዜ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር የጭስ ማውጫውን (flue) ይክፈቱ። ቤትዎን ለማሞቅ የማብሰያ ምድጃዎን በጭራሽ አይጠቀሙ።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የካርቦን ሞኖክሳይድ አላርም ህግ**

ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

አዲሱ ህግ ከ 2008 በፊት የተገነቡ የሲንግል ፋሚሊ፣ የባለ ሁለት ዩኒት ቤቶች እና የታውን ሀውሶች በጋዝ የሚሰሩ መገልገያዎች ፤ የእሳት መሞቅያ ወይም ከቤቱ ጋር የተያያዘ ጋራዥ ካላቸው የካርቦን ሞኖክሳይድ አላርሞችን መግጠም እንዳለባቸው ያዛል። የሜሪላንድ ስቴት ህግ ከጃንዋሪ 2008 ጀምሮ የተገነቡ አዲስ ቤቶች የካርቦን ሞኖክሳይድ አላርም እንዲገጠም ያዛል።

<u>ለነጻ</u> የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ